በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
የሕዝብ ጥናት ማዕከል

# የልደትና የቤተሰብ ሙከራ ጥናት
## የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ

ታህሣሥ 1982

## ማውጫ


አርእስት — ገጽ

I. መግቢያ ........................ 1

1. የልደትና የቤተሰብ ናሙና ጥናት አላማ ........ 2
2. ለጥናት የተመረጠው ሕዝብ ............... 3
3. ለልደትና ለቤተሰብ ናሙና ጥናት የተዘጋጁ መጠይቆች 3
4. የመስክ ሥራ አወቃቀር .................. 4
5. የመረጃ ሰብሳቢ አጠቃላይ ተግባርና ኃላፊነት .... 5
6. የመረጃ ሰብሳቢዎች ሥልጠና ............... 5
7. የመረጃውን ጥራት ለመጠበቅ የሚከናወኑ የቁጥጥር ተግባራት ........................ 7
8. የልደትና ቤተሰብ ናሙና ጥናት ላይ የሚሳተፉ ሁሉ መከተል ያለባቸው መመሪያዎች ............. 7

II. ቃለ መጠየቅ አቀራረብ ..................... 9

ሀ. ከመልስ ሰጪዎች ጋር መግባባት መፍጠር ..... 9
ለ. ስለ ቃለ መጠይቅ አቀራረብ ተጨማሪ ጠቃሚ ነጥቦች 11

III. የመረጃ አሰባሰብ ተግባር ቅደም ተከተል .......... 15

ሀ. ለመረጃ ሰብሳቢ ተግባር የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች 15
ለ. ለጥናት የተመረጡ ቤተሰቦች የሚኖሩበትን ቤት ለይቶ ማወቅ ........................ 17
ሐ. የተሞሉ መጠይቆችን መመርመር ........... 22
መ. ዶክመንቶችንና ዕቃዎችን ማስረከብ ........ 23

IV. የመጠይቅ አሞላል አጠቃላይ መመሪያ ............ 24

ሀ. ጥያቄዎች አቀራረብ .................. 24
ለ. መልሶች አመዘጋገብ .................. 24
ሐ. ስህተቶችን ማረም ................... 26
መ. ትእዛዞችን መከተል .................. 27
ሠ. የተሞሉ መጠይቆችን መመርመር ........... 27

| የቤተሰብ መጠየቅ | ገጽ |
|---|---|
| ሀ. የአካባቢ መለያ ........................ | 29 |
| ለ. የቤተሰብ ዝርዝር ሁኔታ መመዝገቢያ ቅፅ ............ | 29 |
| የቤተሰቡ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጸባዮች መጠይቅ ....... | 31 |
| ሀ. የአካባቢ መለያዎች ........................ | 31 |
| ለ. የቤተሰቡ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጸባይ ጥያቄዎች ....... | 31 |

የቤቶች መጠይቅ

| | |
|---|---|
| 9 የአካባቢ መለያዎች ........................ | 36 |
| ክፍል 1 – የመልስ ሰጭዎች ባሕርያት .............. | 36 |
| ክፍል 2 – የጋብቻ ታሪክ .................... | 42 |
| ክፍል 3 – የልደት ታሪክ .................... | 43 |
| ክፍል 4 – የጤናና የማጥባት ሁኔታ .............. | 47 |
| ክፍል 5 – የወሊድ ቁጥጥር .................. | 49 |
| ክፍል 6 – መውለድ የሚፈልጉቸው ልጆች ብዛት ......... | 62 |
| ክፍል 7 – የባለቤት ባሕርያት ................ | 64 |
| የመረጃ ሰብሳቢ ዕለታዊ የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ .... | 65 |

## 2. ለጥናቱ የሚመረጠው ሕዝብ

ለልደትና ቤተሰብ ናሙና ጥናት ከጠቅላላ የአገሪቱ ክፍሎች /ገጠርና ከተማ/ ወደ 15,000 የሚጠጉ ቤተሰቦች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተመርጠዋል:: ከነዚሁ ቤተሰቦች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ15–49 ለሆኑ ሴቶች /ወደ 15,000 ለሚሆኑ/፣ በጥናቱ ከተመረጡት ሴቶች ባሎች ውስጥ ወደ 1000 ለሚሆኑና ለ500 የከተማ ነዋሪዎችና ገበሬ ማህበራት መሪዎች መረጃ ይሰበሰባል::

## 3. ለልደትና ቤተሰብ ናሙና ጥናት የተዘጋጁ መጠይቆች

ለልደትና ለቤተሰብ ናሙና ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ አምስት መጠይቆች ተዘጋጅተዋል:: እነዚህም የቤተሰብ መጠይቅ፣ ዕድሜያቸው 15–49 ለሆኑ ሴቶች የተዘጋጀ መጠይቅ፣ የባሎች መጠይቅ፣ የከተማ ነዋሪዎች፣ የገበሬ ማህበራት መሪዎችና ለሴቶች ማህበር ሊቀ መናብርት መጠይቅና የአካባቢ ሁኔታ መጠይቅ ናቸው::

ሀ. በቤተሰብ መጠይቅ በቤተሰቡ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ አባላትና በቤት ያደሩ እንግዳ ሥም፣ ባሕሪያትና /ዕድሜ፣ ጾታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ... ወዘተ/ ስለ ቤተሰቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ይሞላል::

ለ. የሴቶች መጠይቅ በሰባት ዋና ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን የሚከተለው መረጃ ለመሰብሰብ እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ ነው::

- ስለሴቶቹ ባሕሪያት /ዕድሜ፣ የትምህርት ሁኔታ፣ የሥራ ሁኔታ፣ ሃይማኖት፣ ... ወዘተ/
- የጋብቻ ሁኔታ /አግብተው ያውቁ እንደሆነ፣ አግብተው የሚያውቁ ከሆነ የጋብቻ ዕድሜ፣ የጥሎሽ ሁኔታ፣ ... ወዘተ/

ሀ. በጥናቱ የተሰማራ ማንኛውም ሰው የሥራ ድርሻ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፤

ለ. በሕመም ሆነ በሌላ ምክንያት ማንኛውም ሰው በሥልጠና ወቅትም ሆነ መረጃውን በማሰባሰብ ጊዜ በቅድሚያ ከተቆጣጣሪው ፈቃድ ሳያገኝ መቅረት ከሥራ ያስወጣል::

ሐ. ሥልጠናን በሚገባ አለመከታተልና አርፍዶ በሥራ ቦታ መገኘት አጥብቆ የተከለከለ ነው::

መ. መረጃ ሰብሳቢዎች የሚመረጡት በክፍሉ ውስጥ በሚያደርጉት ትጋትና በማጠቃለያ ፈተና በሚያገኙት ውጤት ስለሆነ በፈተና ወቅት ከጓደኛው ሲገለብጥ ወይም ጓደኛውን ሲጠይቅ የተገኘ ከሥራ ይታገዳል::

ሠ. መረጃ ሰብሳቢዋ በሥልጠናም ሆነ በመስክ ሥራው ወቅት የመሥሪያ ቤቱ ባልደረባ በመሆን ተቆጥራለች:: ለመረጃው አሰባሰብ ሥራ መቃናት የመልስ ሰጪዎች ትብብር በጣም አስፈላጊ ነው:: ስለሆነም መረጃ ሰብሳቢዋ ከተመደበችበት አካባቢ ነዋሪ ሕዝብ ጋር ተግባብታ የመረጃ አሰባሰቡን ሥራ ማከናወን ይኖርባታል:: የሕዝቡን ድጋፍ ለማግኘት ከአስነዋሪ ድርጊቶች መቆጠብ ያስፈልጋል::

ረ. ለጥናቱ ሥራ መሳካት በቡድኑ ውስጥ የሚገኙ አባላት በመተባበር የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጋራ በመፍታት መረዳዳት ይኖርባቸዋል::

በቡድኑ ውስጥ ችግርና አለመግባባትን የሚፈጥር አባል ካለ በልደትና በቤተሰብ ናሙና ጥናት ዲሬክተር ውሳኔ መሠረት ከሥራ ይሰናበታል::

ሰ. የሚሰበሰበው መረጃ ጥራትና ትክክለኛነት በጣም አስፈላጊ ስለሆነ፤ ይህንንም የሚያሟላ መረጃ እንዲሰበሰብ በየጊዜው ቁጥጥር ይደረጋል:: በማንኛውም ወቅት መረጃ ሰብሳቢዋ ጥራት ያለው መረጃ ለመሰብሰብ ዝግጁ ሆና ባልተገኘች ከሥራ ትሰናበታለች::

፭. የሚጠበቀን መልስ በቅድሚያ አለመገመት

መልስ ሰጪዎች ስለሚናገሩት ችሎታ ወይም ዕውቀት በቅድሚያ ለገምቱ ይሆናል ብሎ ማሰብ አያስፈልግም:: በገጠር የሚኖሩ ወይም ያልተማሩ ሰዎች ስለሰሚሉት ቀጥተኛ ወይም ስለዘዴዎች ምንም እንደማያውቁ አድርጎ መገመት የለበትም:: በመልስ ሰጪና በመረጃ ሰብሳቢ መካከል ልዩነት መፍጠር ቃለ መጠይቁ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል:: መልስ ሰጪ ለረጃ ሰብሳቢ ከሱ የተለዩ ለአርጋ ማሰብ መቀበትን ወይም ግርግርን ሊያስከትል ይችላል:: ስለዚህ በትሁት መንገድ መልስ ሰጪን ሊያስናንትና በግልጽ መናገር በሚችልበት ሁኔታ ቃለ መጠይቁን ማካሄድ ያስፈልጋል::

፮. ቃለ መጠይቁ በሚደረግበት ወቅት አለማቻኮል

ጥያቄው ለመልስ ሰጪና ግልጽ እንዲሆን ረጋ ብሎ ማንበብ ያስፈልጋል:: ጥያቄውም ከቀረበ በኋላ አስቦ መመለስ የሚችልበት ጊዜ እንዲኖረው ፋታ መስጠት ያስፈልጋል:: መልስ ሰጪዎችን ማቻኮል "አላውቅም" በማለት ወይም ተገቢ ያልሆነ መልስ እንዲሰጡ ይገፋፋቸዋል:: መልስ ሰጪዎች ቃለ መጠይቁን በቀጥተኛ ለመቀበል የማይችሉበት ሁኔታ ካጋጠመ "የሚያስቸግር ነገር የለም፤ የሚፈልጉት ሀሳብ በደንብ ጠቃሚ ስለሆነ ረጋ ብለው አስበው ለመመለስ ይሞክሩ" በማለት ለማረጋጋት መሞከር ያስፈልጋል::

5. ለመስክ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ዶኩሜንቶችና ዕቃዎች መረከብ

የመረጃ ሰብሳቢ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ለመረጃ ሰብሳቢው የሚያስፈልጉትን ዶኩሜንቶችና ዕቃዎች መረከብ ያስፈልጋል:: ለመረጃ ሰብሳቢው ሥራ የሚያስፈልጉ ዶኩሜንቶችና ዕቃዎች ዝርዝር:-

- ለጥናት የተመረጡ ቤተሰቦች ዝርዝር።
- የቤተሰብ መጠይቅ።
- የቤቶች መጠይቅ።
- የቤቶች መጠይቅ ማጠቃለያ ቅጽ።
- የመረጃ ሰብሳቢ መመሪያ።
- የመረጃ ሰብሳቢ ዕለታዊ የሥራ ክንውን መግለጫ ቅጽ።
- የጥናት ክልል የሚያሳይ ካርታ ከነመግለጫው።
- የመረጃ ሰብሳቢ ቦርሳ።
- እርሳስ ላጲስ ... ወዘተ።
- የመታወቂያ ባጅ።
- ሌሎች የግል መገልገያ ዕቃዎች መረጃ ሰብሳቢው እንደ ተመደበበት አካባቢ ሁኔታ የሚሆኑ።

## 2.5 የቤተሰብ ኃላፊ መቀየር ሊያጋጥም ይችላል

የቤተሰብ ምዝገባ ከተካሄደ በኋላ የቤተሰብ ኃላፊ መኖሪያ ሊቀይር ወይም ሞቶ ሊሆን ይችላል:: ይህ ሁኔታ ካጋጠመ በቤቱ ለሚኖረው ቤተሰብ መጠይቆች ይሞላሉ::

## 2.6 ቤቱ ተዘግቶ ምንም ሰው ካልተገኘና ጎረቤቶች ቤተሰቡ ዘመድ ጥየቃ ወይም ለሥራ ለረጅም ጊዜያት የሄዱ መሆናቸውን ከታወቀ

ቤተሰቡ የሌለ መሆኑን በመግለጽ በዕለታዊ የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቀጽ በመጠይቁ ላይ መሙላት ያስፈልጋል::

## 2.7 ቤቱ ዝግ ከሆነና ጎረቤቶች ቤተሰቡ ወደ ሌላ ቦታ ለቋሚ የሄዱ መሆናቸውን ከገለጹ

ቤቱ ባዶ መሆኑን በቀጽና በመጠይቁ ላይ መሙላት ያስፈልጋል::

## 2.8 የተመረጠው ቤት ድርጅት ሆኖ ከተገኘና ማንም ሰው የማይኖርበት መሆኑ ከተረጋገጠ

ቤቱ ማንም የማይኖርበት ወይም ድርጅት መሆኑን መመዝገብ ያስፈልጋል::

## 2.9 የተመረጠው ቤት ተቃጥሎ ወይም ፈርሶ በቀበሌው ወይም በገበሬው ማህበር ክልል ካልተገኘ

ሁኔታው በመጠይቁ በቀጽ ላይ መግለጽ ያስፈልጋል::

ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች በሚያጋጥሙበት ወቅት ለተቆጣጣሪው ሪፖርት ማቅረብ ያስፈልጋል:: በተለይ በ "2.1"ና በ"2.6 - 2.9" በተመለከቱት ምክንያቶች ለዋናው የተመረጠው ቤተሰብ ባይገኝ በምትኩ ሌላ ቤተሰብ መርጦ እንዲ በት ለተቆጣጣሪው ሁኔታውን ማሳወቅ ይገባል::

3. <u>የሴቶች መጠይቅ የሚሞላባቸውን ቤቶች መለየት</u>

የሴቶች መጠይቅ የሚሞላው ዕድሜአቸው ከ 15 – 49 ለሆኑትና መደበኛ የቤተሰብ አባላት ነው:: ይህም በትዳር ላይ የሚገኙትንና አግብተው የሚጸዉቁትንም ሴቶች ያጠቃልላል:: ከቤተሰቡ ለሚገኙ እንግዶች ይህ መጠይቅ አይሞላባቸውም:: መደበኛ የቤተሰብ አባል ከሆኑት መካከል በተለያዩ ምክንያቶች /ለቅሶ፣ ሠርግ ወዘተ./ በቤታቸው ለማይገኙ አባላትም ጭምር መጠይቁ መሞላት ይኖርበታል:: ነገር ግን እነዚህን ሴቶች ማግኘት ካልተቻለ፣ ሊገኙ ያልተቻለበትን ምክንያት ተገልጾ መጠይቁ ባይሞላ ይታለፋል::

ቃለ መጠይቁ ከመከናወኑ በፊት መጠይቁ ለሚሞላባቸው ሴቶች በቤቶች መጠይቅ ቅፁን ላይ በተገቢው ቦታ የአካባቢ መለያ መሞላት ይኖርበታል:: ቃለ መጠይቁን በሆነ ምክንያት ማጠናቀቅ ካልተቻለ በመጠይቁ ቅፁን ላይ "ውጤት" በሚለው ትክክለኛ ምክንያቱ ይጻፋል:: በድጋሚ ጉብኝት ለማድረግ ቀጠሮ መያዝ ያስፈልጋል::

የሴቶች መጠይቅ የሚሞላባቸውን ሴቶች ለመለየትና እንዲሁም መጠይቁን ለመሙላት ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጥቂቶቹ:-

- የሴቶች መጠይቅ የሚሞላባቸው ማለትም ዕድሜያቸው ከ15 – 49 የሆኑ የሌለበት ቤተሰብ ሊያጋጥም ይችላል:: ለዚህ ቤተሰብ የቤተሰቡ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጸባዮች መጠይቅ ይሞላና የሴቶች መጠይቅ አይሞላለትም ማለት ነው::

ግለሰቧን ለማግኘትና ዓለትም ቃለ መጠይቅ ለማድረግ የተደረገው ሙከራ መዘረዝር ሙሉ በመረጃ ሰብሳቢና ዕለታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት በዓምድ –10 ላይ ይመዘገባል:: ይህም መረጃ በሌሎትና ቤተሰብ ዋናት ቀን ያሉ ግለሰቦች መጠይቅ እንደ ተምሳሳቸው ለመገምገም ይረዳል:: ስለዚህ ይህ ቅጽ ቅጠሩ እንዳበቃ ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት ይመለሳል::

ሠ. የተሞሉ መጠይቆችን መመርመር

ቃለ መጠይቅ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ መረጃውን በትክክል መሟላቱን መመርመር የመረጃ ሰብሳቢ ኃላፊነት ነው:: ለዚያው የተሰበሰበትንና ባተ ሁሉ መጠየቅ ያለባቸው ጥያቄዎች በሙሉ መጠየቃቸውን፣ መልሶቹ ግልጽና የሚነበቡ መሆናቸውንና መልሶች እርስ በርስ የማይቃረኑ መሆናቸውን በሚገባ ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ግለሰቧን የማይመለከቱ ጥያቄዎች በመመሪያው መሠረት መዘለላቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በመረጃ ሰብሳቢና መታረም የማይችሉ ስህተቶች ቢያጋጥሙ ግለሰቧን ይቅርታ በመጠየቅ ስህተቱ መታረም አለበት::

መጠይቆችን መገልበጥ አያስፈልግም:: መረጃውን ወደ ሌላ መጠይቅ መገልበጥ ስህተቶችን ሊፈጥር ይችላል:: ስለዚህ የመጠይቁን ንጽሕና ለመጠበቅ ሲባል መረጃዎችን በሌላ ወረቀት ላይ ጽፎ ወደ መጠይቅ መገልበጥ ስህተት መፍጠር ስለሚሆን ወዲያውኑ የተሰጠውን መረጃ በመጠይቁ ላይ መሙላት አለበት:: መረጃውን ለመሙላት ስሌት ማድረግ ካስፈለገ በሌላ ወረቀት ላይ ማድረግ ይቻላል:: ለየት ያለ መልስ ቢኖር አስተያየት መጻፍ ካስፈለገ በጥያቄው አጠገብ ወይም አስተያየት መስጫ ቦታ ባለ በአስተያየት መስጫው ቦታ መጻፍ ይገባል:: እነዚህ አስተያየቶች ለተቆጣጣሪው ወይም ለመስክ ሊቪተሩ መጠይቁን በሚያርሙበት ወቅት ሊረዳቸው ይችላል::

ሠ. ደብዳቤዎችና ዕቃዎችን ማስረከብ

የመረጃ አሰባሰቡ ሥራ እንደተጠናቀቀ ለሰፈሰገ የሆኑ ደብዳቤዎችን ለተቋማቸው ማስረከብ ያስፈልጋል። ይኸውም የመረጃ ሰብሳቢ ለቦታው ቀበሌ/ገበሬ ማኅበር ሊቀመንበር የሚያስረክበው የመረጃ አሰባሰብ ሥራ እንደተፈጸመ ቤቱ ለሱ እንዲረከቡ ቢተባበሩ በሙሉ መረጃ ውስጥ በቦታ የቤተሰብ መጠይቆችና የቤ ቶች ዝርዝር ቅጽ እንዲሁም የቤቶች ዝርዝር ቅጽ የመረጃ ሰብሳቢ ተቆጣጣሪ የሥራ ክንውን ሪፖርት መመዝገቢያ ቅጽ በቅጽ በተራ ሁኔታ ወጪ ቀሪን ካረጋገጡ በኋላ ለተቋማቸው ማስረከብ አለባቸው።

1. ኮድ የተሰጣቸው መልሶች ያሏቸው ጥያቄዎች፦ መልስ ለመመዝገብ፣ ለእነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ከእያንዳንዱ ጥያቄ ቀጥሎ ባለው ቦታ አማራጭ መልሶች ከነኮዳቸው ቀርበዋል ። መልስ ሰጪዎ ለሰጡቸው መልስ ተስማሚ የሆነውን ኮድ በመከበብና ኮዱን በተሰጠው ሣጥን ውስጥ በመጻፍ መረጃውን ይመዘግባሉ ።

<u>ምሳሌ</u>

| ተራ ቁጥር | ጥ ያ ቄ |
| --- | --- |
| 301 | አግብተው ያውቃሉ ወይንም ከወንድ ጋር ኖረው ያውቃሉ?<br>① አዎን /1/ 2. የለም / /<br>/ወደ 325 ይለፉ/ |

ስለዚህ ለጥያቄ "301" መልሱ አዎን በለሆነ አዎን ለሚለው መልስ ኮድ "1" በመሆኑ በተሰጠው ባዶ ሣጥን ውስጥ "1" የሚል ኮድ ገብቷል ።

አንዳንዱ ጥያቄዎች "ሌላ" የሚል አማራጭ መልስ ያላቸው ናቸው ። የተሰጠው መልስ በተዘረዘሩት መልሶች ውጪ ከሆነ "ሌላ" ለሚለው የተሰጠውን መልስ ባለው ክፍት ቦታ በመመዝገብ "ሌላ" ለሚለው የተሰጠውን ኮድ በሳጥኑ ውስጥ ማስገባት ነው ።

<u>ምሳሌ</u>

| ተራ ቁጥር | ጥ ያ ቄ |
| --- | --- |
| 127 | የቤቱ ወለል አብዛኛው የተሠራው ከምንድን ነው?<br>1. ከአፈር / /<br>2. ከሲሚንቶ / /<br>3. ከድንጋይ/ሸክላ/ / /<br>4. ከፕላስቲክ ንጣፍ / /<br>5. ከእንጨት / /<br>⑥ ከሌላ /ይገለጽ/ <u>ባጠራ</u> /6/ |

ምሳሌ

| ተራ ቁጥር | ጥ ያ ቄ |
|---|---|
| 216 | ሬዲዮ አዳምጠው ያውቃሉን ?<br>1. አዎን ② የለም /2/<br>/ወደ 218 ይታለፉ/ |

መ. ትእዛዞችን መከተል

"ወደ_____ ይታለፉ" ወይም "_____ጥያቄ ይጠየቅ" የሚሉ ትእዛዞች

መልስ ሰጪዎን የማይመለከቱት ጥያቄ ላለመጠየቅ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ::. ለምሳሌ ነፍሰ ጡር ያልሆነችን ሴት የስንት ወር ነፍሰ ጡር እንደሆነች መጠየቅ አግባብ አይደለም ::እንዲያውም እንዲህ አይነቱ ሁኔታ መልስ ሰጪዎችን ሊያስቀይም ወይም ሊያስቆጣ ይችላል :: ቀጥሎ ያለው ጥያቄ መጠየቅ ከሌለበት ለጥያቄዎች ከቀረቡ መልሶች አጠገብ ወደ ሌላ ጥያቄ መተላለፍ እንደሚገባ የሚገልፅ ትእዛዞች ተሰጥተዋል :: ስለዚህ መጠየቅ የሌለባቸው ጥያቄዎች እንዳይቀርቡ እነዚህን ትእዛዞች በሚገባ መከተል ያስፈልጋል ::

ምሳሌ

| ተራ ቁጥር | ጥ ያ ቄ |
|---|---|
| 423 | በአሁኑ ወቅት ነፍሰ ጡር ነሽን?<br>1. አዎን / / ② የለም /2/<br>3. እርግጠኛ አይደለሁም / /<br>/ወደ 428 ይታለፉ/ |

ለተሰጠው ጥያቄ የተሞላው ኮድ "2" ነው ማለትም ግለሰቧ ነፍሰ ጡር አይደለችም :: ስለዚህ ጥያቄ 424–427 የሚጠየቁት ነፍሰ ጡር ለሆኑ ብቻ ስለሆነ ነፍሰ ጡር ላልሆኑ ሴቶች ጥያቄዎቹ ይታለፋሉ ማለት ነው ::

ሠ. የተሞሉ መጠይቆችን መመርመር

ቃለ መጠይቁ እንደተጠናቀቀ መረጃ ሰብሳቢዋ እያንዳንዱን ጥያቄ በማየት መጠይቁ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ ይኖርባታል :: መጠየቅ ያለባቸው ጥያቄዎች ስለመዘለላቸውና 'ወደ________ ይታለፉ' የሚሉ ትእዛዞችን በሚገባ መከተሏን መመርመር አለባት ::

ግልፅ ያልሆኑ መልሶች ወይም የማይ ነበቡ ጽሑፎችን ማስተካከል ያስፈልጋል ። መልስ በጪቀን በድጋሚ ማግኘት ቀላል ስለማይሆን ወደ ሌላ ቤተሰብ ከመሄድ በፊት አዛው ለ ያሉ መጠይቅን በጥንቃቄ በተሰጡት መልሶች በመመርመር አስፈላጊውን ማድረግ የተሻለ ይሆናል ።

መረጃው አቀባይ ላይ ግልፅ ያልሆነ ነገር ካለ ማስታወሻ ጥያቄው አጠገብ በመጻፍ ተቆጣጣሪውን ማማከር ያስፈልጋል ።

ለምሳሌ በአንድ ቤተሰብ የሚገኙት ጠረጴዛዎች ብዛት አሥር ቢሆን የሚመዘገበው "8" ነው ማለት ነው ::

129. ቤተሰቡ ባለፈው ዓመት በአብዛኛው በምግብነት ያዋለውን ቀለብ ያገኘው አምርቶ ወይንም ሸምቶ እንደሆነ በመለየት ኮዱ ይመዘገባል ::

130 የቤተሰቡን የዓመት ገቢ ለማወቅ ያስችል ዘንድ የተለያዩ የገቢ ምንጭ ዐይነቶች ተዘርዝረዋል :: ስለዚህ ቤተሰቡ የዓመት ገቢው ምን ያህል እንደሆነ በመጠየቅ በየምንጮቹ አኳያ ብዛቱ በብር ይገለጻል :: እዚህ ላይ የአንድ ቤተሰብ የገቢ ምንጮች አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል :: የገቢው መጠን በብር ሲመዘገብ ሳንቲሞችን እንደማይጨምር መገንዘብ ያስፈልጋል ::

202– መልስ ሰጭ ዕድሜአቸውን ቅበይ ቶው የጨረሱት ሙሉ ዓመት ይመዘገባል ። ይህም ማለት ከተወለዱ 32 ዓመት ከአሥር ወር ለሆናቸው የሚሞላላቸው 32 በቻ ነው ። አንዳንድ ሴቶች ዕድሜአቸውን በትክክል ለመናገር የማይችሉ ሊያጋጥሙ ይችላል ። በዚህን ወቅት የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ዕድሜአቸውን ለመገመት ጥረት መደረግ ይኖርበታል ። የተወለዱበትን ዓመትና ወር ሲጠየቁ በትክክል ለመመለስ ላልቻሉ ሴቶች ከላይ በተመለከተው ጥያቄ 201 መልስ ባለማግኘትበደውን ሲተው ለጥያቄ 202 ግን የግድ መልስ ማግኘት አስፈላጊ ነው ። ዕድሜአቸውን ለመናገር ለሚያስቸግራቸው ሴቶች ዕድሜአቸውን ለመገመት ከሚያስችሉት ዘዴዎች መሀከል፤

ሀ. ዕድሜአቸውን ከአንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች ጋር አያይዘው መናገር የሚችሉ ከሆነ በመጠየቅ ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ የቀረበውን የታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር በመመልከት ዕድሜአቸውን መገመት፤

ለ. ሌሎች ዕድሜአቸውን ከሚያውቁ የቤተሰብ አባላት ወይንም የአካባቢው ሰዎች ጋር አያይዘው ዕድሜአቸውን መናገር ይችሉ እንደሆነ በመጠየቅ ዕድሜአቸውን መገመት፤

ሐ. ካገቡ ወዲህ ምን ያህል ጊዜ እንደሆናቸውና ሲያገቡ ምን ያህል ዕድሜ እንደነበራቸው ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ ዕድሜአቸውን መገመት፤

መ. የመጀመሪያ ልጃቸውን ከወለዱ ምን ያህል ጊዜ እንዳለፈና የመጀመሪያውንልጅ ሲወልዱ ዕድሜአቸው ስንት ዓመት እንደነበረ በመጠየቅ መገመት ያስፈልጋል ።

በዚህ ጥያቄ አማካይነት የሚገኘው የሴትየዋ ዕድሜ መረጃና በጥያቄ 201 የተመዘገበው ሴትየዋ የተወለዱበት ዓመትና ወር የማጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ።

208. ትምህርት በመከታተል ላይ ያሉ የሚባሉት በመደበኛ ት/ቤት ገብተው በመማር ላይ የሚገኙ፣ በመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ተመዝግበው ትምህርትን በመከታተል ላይ የሚገኙ፣ የጎልማሶች ትምህርት በመማር ላይ የሚገኙ፣ ከጓደኛ ወይንም ከዘመድ የሚሰጥ ትምህርት ወይንም ሌላ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በመከታተል ላይ ያሉትን ነው።

209. መደበኛ ትምህርት የሚባለው ተማሪዎች ትምህርትን ለመከታተል ተመዝግበው፣ የትምህርት ፕሮግራም ወጥቶለት፣ ትምህርትን ለመከታተል ለተመዘገቡ ተማሪዎች በየወቅቱ መመዘኛ ፈተና እየተሰጠ ፈተናውን በማለፍ ወደ ሚቀጥለው ክፍ ወደ ሌላ የትምህርት ክፍል ወይም ትምህርት እየተዘዋወረ ትምህርት የሚከታተሉበት ሥርዓት ያለው የትምህርት ፕሮግራም ነው።

210. የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ተብሎ የሚመዘገበው የደረሱበት ከፍተኛ ክፍል ሳይሆን ተምረው ያጠናቀቁ ከፍተኛ ክፍል ነው። ለምሳሌ አራተኛ ክፍልን አጠናቀው አምስተኛ ክፍል ለጀመረ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል የሚባለው አራተኛ ክፍል ነው። አሥራ ሁለተኛ ክፍል አጠናቀው መደበኛ በሆነ በዩኒቨርሲቲ ፕሮግራም ወይም ሌላ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ትምህርት ለተከታተሉ ያጠናቀቁ ዓመት ብዛት እና የትምህርቱ ዓይነት ይመዘገባል። ለምሳሌ 2ኛ ዓመት በማትማቲክስ ያጠናቀቁ፣ 4ኛ ዓመት በመሀንዲስና BA ወይም BSC ... ወዘተ. በዚህ ጥያቄ ሰባተኛ ክፍልና ከዚያ በላይ የጨረሱ ሁሉ ወደ ጥያቄ 214 ሲያልፉ ከዚያ በታች ትምህርት ያገኙ ግን ወደ ጥያቄ 216 አልፈው ስለማን በብና መጻፍ ችሎታቸው ጥያቄ ይቀርብላቸዋል።

213. የመሠረተ ትምህርትን ፕሮግራም በሚገባ ያጠናቀቀ ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያት የምስክር ወረቀትን ያልተቀበሉ የምስክር ወረቀት እንደተቀበሉ ይቆጠራሉ።

237. ከረመዳን ወር ጾም ውስጥ ከግማሽ በላይ የሆነውን የሚጾሙ ኮድ 1 ሲመዘገብላቸው ከዚያ ላነሱ ቀናት ለሚጾሙ ኮድ 2 ይመዘገባል ::

## ክፍል 2 — የጋብቻ ታሪክ

301. ከወንድ ጋር ይኖራሉ የሚባሉት፣ የጋብቻ ሥነ ስርዓት ባይፈጽሙ እንደባልና ሚስት ሆነው አንድ ላይ በአንድ ቤት የሚኖሩ ግለሰቦች ናቸው :: በቤተኛ አዳሪነት የሚኖሩና ከብዙ ወንዶች ጋር ግኑኝነታቸውን የሚያሳልፉት፣ ከወንድ ጋር እንደሚኖሩ አይቆጠርም :: የጋብቻ ሥርዓት ሳይፈጽሙ ከወንድ ጋር መኖር በአንዳንድ አካባቢዎች አስነዋሪ ድርጊት በመሆኑ ይህንን ጥያቄና በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን ጥያቄዎች ለመልስ ሰጭዎች በምናቀርብበት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል :: ምክንያቱም በነዚህ ጥያቄዎች ምክንያት ከሴቶች ጋር አለመግባባት ቢፈጠር ለተከታዮቹ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ለማግኘት ስለሚያስቸግር ነው ::

303. ባልና ሚስት በተለያዩ ቦታዎች የሚኖሩት በሥራ፣ በግዳጅ፣ በትምህርት፣ ወዘተ ምክንያት ሊሆን ይችላል ::

311. የጥሎሹን ዋጋ ለመተመን አስቸጋሪ በመሆኑ በትክክል ለማወቅ ቢያዳግትም ግምቱን ማግኘት የግድ ያስፈልጋል :: /ልብስ/ ጌጣጌጥ፣ ከብት ወዘተ በብር በሚተመንበት ወቅት በዛሬ ዋጋው ሳይሆን በዚያን ወቅት በአካባቢው በነበረው ዋጋ መሆን ይኖርበታል ::

314. ጋብቻው የተፈጸመበት ወርና ዓመት በአጭሩ ተጠቅሶ ይመዘገባል :: ለምሳሌ ጋብቻው የተፈጸመው በጥቅምት ወር 1976 ከነበረ የሚመዘገበው በወሩ ሣጥን 02፣ በዓመቱ ሣጥን 76 ይሆናል ማለት ነው:: ይህን ጥያቄ በቀላሉ ለመመለስ የሚያዳግታቸው ሴቶች ካጋጠሙ ከሚቀጥለው ጥያቄ የሚገኘው መልስ ሊረዳ ይችላል ::

በአሁኑ ጋብቻ ውስጥ የተገኙትን ልጆች ብቻ ሳይሆን በሌሎች ጋብቻዎችም የተወለዱትን ያጠቃልላል ። በተለይም ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆች እንዳ ይረሱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ።

401. ይህ ጥያቄ ከዚህ በፊት በጋብቻ ላይ ለነበሩና ትዳር መስርተው ለማያውቁ ሴቶች ጭምር ይጠየቃል ። ትዳር መስርተው የማያውቁ ልጃገረዶች ልጅ ወልደው እንደሆነ ሲጠየቁ ቅር ሊሰኙ ስለሚችሉ ጥያቄው በሚቀርብበት ወቅት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ።

402. ከሴትየዋ ጋር የሚኖሩ ልጆች የሚባሉት ሴትየዋ ከምትኖርበት ቤት ውስጥ በአንድነት አብረው የሚኖሩ ልጆች ናቸው ።

406. ከሴትየዋ ጋር የማይኖሩ ልጆች የሚባሉት ሴትየዋ ከምትኖርበት ቤት ውጭ የግላቸውን ትዳር መሥርተው የሚኖሩ፣ ለሥራ በሌላ ቦታ የሚገኙ፣ ለትምህርት በሌላ አካባቢ የሚገኙ፣ እና የሞቱባት ናቸው ።

410. ሴትየዋ ከወለደቻቸው ልጆች መካከል የሞቱትን ለማስታወስ ደስ የማይላት ስለሆነ ስለምትችል ጥያቄው በሚቀርብበት ወቅት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ። በተለይ ሴቷ ከሞተባቸው ሴቶች መካከል ብዙ ሴቶች አለሞተባትም የሚል መልስ ሊሰጡ ስለሚችሉ ትክክለኛውን መልስ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል ።

411. ሴቶች የሞተባቸውን ልጆች ብዛት በሚጠየቁበት ወቅት ሙሉ ፈቃደኛ ሆነው ላይገኙ ስለሚችሉና የሞተባቸውን ልጆች ብዛት ቀንሰው ሊያቀርቡ ስለሚችሉ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ።

ወቅት እንደሆነ በመጠየቅ ለመገመት ይቻላል ። ዕድሜአቸው አምስት ዓመት ሳለፋቸው ልጆች የተወለዱበት ወር በትክክል ባይታወቅ ዓመቱ ብቻ ሊመዘገብ ይችላል ። ከአምስት ዓመት በታች ለሆናቸው ልጆች ግን አስፈላጊው ሙከራ ተደርጎ ልጁ የተወለደበት ወርም መገኘት አለበት ። እንዲሁም የልጁ ዕድሜ ሲመዘገብ ከሁለት ልጆች መካከል ያለው የዕድሜ ልዩነት ረጅም ከሆነ/ለምሳሌ ሦስት ዓመት ወይንም ከዚያ በላይ/ በሕይወት የተወለደ ልጅ በሁለቱ ልጆች መካከል እንደነበረ ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል ።

418. ልጁ የተወለደው ከገንት ዓመት በፊት እንደሆነ ወይንም የልጁ ዕድሜ በንት እንደሆነ የሚሰጠው መረጃ ከጥያቄ 417 ጋር መመሳከር አለበት ።

420. የሞቱ ልጆች ዕድሜ በሚመዘገብበት ወቅት ሲሞቱ ዕድሜአቸው አንድ ወር ያልሞላቸው ሕፃናት ዕድሜ በቀን በዓምድ 420A ይመዘገባል ። አንድ ወርና ከዚያ በላይ የሆናቸው ነገር ግን ሁለት ዓመት ያልሞላቸው ልጆች ዕድሜ በጨረሱት ሙሉ ወር በዓምድ 420B ይመዘገባል ። ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው ልጆች ዕድሜ ግን የሚመዘገበው በጨረሱት ሙሉ ዓመት ብቻ በዓምድ 420C ይሆናል ። ምሳሌ፣

| ሲሞቱ የነበራቸው ዕድሜ | ምዝገባ 420 A | 420 B | 420 C |
|---|---|---|---|
| ሀ. ሰባት ቀናት | 07 | — — | — — |
| ለ. አንድ ወር ከሰባት ቀናት | — — | 01 | — — |
| ሐ. አራት ወር ከሰባት ቀናት | — — | 04 | — — |
| መ. አንድ ዓመት ከሶስት ወር ከሰባት ቀናት | — — | 15 | — — |
| ሠ. ሁለት ዓመት ከሶስት ወር | — — | — — | 0. |
| ረ. አምስት ዓመት ከስድስት ወር | — — | — — | 05 |

በዚህ ጥያቄ አማካይነት አሁንም በመጥባት ላይ እንዳሉ
የተገለጸላቸው ሕፃናት ከእናታቸው ጡት ሌላ ይጠጡ እንደሆነ ለማ
ወቅ ወደ ጥያቄ 508 ሲታለፍላቸው ለሌሎቹ ሕፃናት ግን ወደ ጥያቄ
510 ይታለፋል ::

508. ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በጥያቄ 506 አሁንም በመጥባት ላይ እንደ
ሚገኙ ለተገለጸላቸው ሕፃናት ብቻ ነው :: ሕፃናት እደገ በሚሎበት
ወቅት ከእናት ጡት በተጨማሪ ሌላ ምግብ እንዲሰጣቸው ይደረጋል ::
እነዚህ የምግብ አይነቶች ሁሉም በየቀኑ የሚቀርቡ ላይሆኑ ይችላሉ ::
ሕፃኑ ከተዘረዘሩት የምግብ አይነቶች ውስጥ በትላንትናው ዕለት ለተ
ሰጡት የምግብ አይነቶች ኮድ 1 ይከበባል :: በትላንትናው ዕለት
ላልተሰጡት የምግብ አይነቶች ሁሉ ኮድ 2 መከበብ ይኖርበታል ::
ይህ የምግብ አይነት በሌሎች ጊዜያት ይሰጡት የነበረ ቢሆንም በት
ላንትናው ዕለት ምግቡ ያልተሰጠው ከሆነ ኮድ 2 ይመዘገባል ::
በጥያቄው የቀረቡት ሰባቱም የምግብ አይነቶች እንደተለያዩ ጥያቄዎች
እንዲጠእንድለመለስ ሰጥቶ ቅርበው መልስ ማግኘት ይኖርባቸዋል ::

509. ተጨማሪ ምግብ ተብሎ የሚጠቀሰው በአጋጣሚ ወይንም ለመድኃኒትነት
ለአንድ ወይንም ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ምግብ ሳይሆን በምግ
ብነት ታስቦ ለልጁ እድገትና ጤንነት እንዲረዳ እየተደጋገመ የሚሰጥ
የምግብ አይነት ነው ::

510. በዚህ ጥያቄ መውለድ የሚችሉትንና መካን የሆኑትን ሴቶች ለይቶ
ለማወቅ ይሞከራል :: ከዚህ በፊት አገብተው የማያውቁ ከወንድ
ጋር ምንም አይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽመው የማያውቁ ለመ
ውለድ መቻል ወይንም አለመቻላቸውን ላያውቁ ይችላሉ ::

605. በጥያቄ 604 ላይ ሴቶች የሚያሠሯቸውን ዘዴዎች ሁሉ በዝርዝር የገለጿቸው ቢሆን በዚሁ ጥያቄ ደግሞ የተቀሩት ዘዴዎች በሰው እየተጠሩ ሴቶች ስለዘዴዎቹ በስማቸው ለገደሆነ የሚቀበሏቸው በዝንታ ሆኖ ስለ እያንዳንዱ ዘዴ በሬ የሆነ ገለጻ ማቀረብ ያስፈልጋል:: ይህ ጥያቄ በ604 ላይ ሴቶች እንደሚያሠሯቸው ለጠቀሷቸው ዘዴዎች አይቀርብም:: በ604 ላይ ያልተጠቀሱ ዘዴዎች በዝርዝር እየቀረቡ ሴቶች ስለዘዴዎቹ የሚያውቁ ከሆነ ኮድ 1 ቢከበቡ ዘዴዎችን ሴቶች የማያውቁ ከሆነ ኮድ 2 ይከበባል:: ይህ ጥያቄ በተለማሪ የሚቀርበው በ603 ላይ ስለ አንድም ዓይነት ዘዴ በስማቸው ለማያውቁ ሴቶች ብቻ ይሆናል:: የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ተብለው የሚቀርቡት የሚከተሉት ናቸው::

01. ኪኒን ወይንም ፒል የሚባለው ሴቶች ለወሊድ መቆጣጠሪያነት በየቀኑ የሚወስዱት ቋሊት ነው::

02. ኮንዶም የሚባለው በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ወንዶች በብልታቸው ላይ የሚያጠልቁት አንድ ኪስ የሆነ ከላስቲክ የተሠራ ነው:: በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት የሴንድ የዘር ፍሬ በላስቲኩ ኪስ ውስጥ በመፍሰስ እዚያው የሚቀር በመሆኑ ሴቷ ዘሩ በሴት ውስጥ ስለማይደርስ ሴቷን እንዳታረግዝ ይከላከላታል::

03. ሉፕ ወይም አይ ዩ ዲ የሚባለው በሴቷ ማኅፀን ውስጥ በሐኪም ወይንም በሌላ የሕክምና ሠራተኛ አማካይነት የሚቀመጥ ነው:: ይህ ሉፕ ከሴቷ ማኅፀን ለበቂ ጊዜ እንዳታረግዝ መከላከያ ይሆናታል::

04. በኦፕሬሽን ሴቶችን እንዲመክኑ የሚደረገው የሴቷ ዕንቁላል የሚገኝበት ቦታ ወደ ማኅፀኗ እንዲደርስ የሚረዳውን ቧንቧ /ቱቦ/ በመቁረጥ ዕንቁላሉ ወደ ሴቷ ማኅፀን እንዳይደርስ በማድረግ እንዳታረግዝ ይከላከላታል::

05. በስፕሬሽን ወንዶች እንዲመከቱ የሚደረገው የወንድ የዘር ፍሬ ከሚፈጠርበት ከፍል ወደ ብልት የሚያመራውን ቧንቧ /ቱቦ/ በመቁረጥ የዘር ፍሬው ወደ ብልት እንዳይደርስ በማድረግ ግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚያደርጉበት ወቅት የዘር ፍሬው ወደ ሴትዮዋ ብልት ስለማይደርስ እርግዝናን ይከላከላል::

06. መርፌ (injectables) ቅባለው የሚሰጥ ቀጥታ በሴቷ ቆዳ ስር /ለምሳሌ በክንዷ ላይ/ የሚቀበሩ መርፌ የሚመስሉ መድሐኒቶች ሲሆኑ በነዚህም ምክንያት ለተወሰኑ ዓመታት ሴትዮዋ ለማርገዝ መከላከያ ይኖራታል::

07. የማሕፀን ቆብ /ዲያፍራም/ ሴትዮዋ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት በማሕፀንዋ ውስጥ የምታስቀምጠው ቆብ ሲሆን ይህም ቆብ የወንድ የዘር ፍሬ ወደ ማሕፀንዋ እንዳያልፍ ስለሚከላከል እንዳታረግዝ ይረዳታል:: ከቆቡ ጋር በተጨማሪ ፎም ወይም ጄሊ የሚባሉ የወንድን የዘር ፍሬ የሚገድሉ (spermicide) መጠቀም የማርገዝ ዕድሏን በበለጠ ይቀንሰዋል::

08. በቀን መቁጠር እርግዝናን መከላከል፣በወር ውስጥ ሴትዮ የማያረግዙበት ቀናት ብቻ የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ማድረግ /ቀን አቆጣጠር/ የሚባሉ ሴቶች በወር ውስጥ የሴትዮዋ ዕንቁላል በማሕፀንዋ በሚገኝበት ወቅት ወይንም ወደ ማሕፀንዋ ሲያልፍ ሦስት ቀናት ሲቀረው ድረስ የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ባለመፈጸም እርግዝናን የመከላከል ዘዴ ነው::

09. የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ከማድረግ መቆጠብ (abstinence) በሠሊጥ መቁጠሪያ ዘዴነት የሚቆጠረው ሴትዮዋና ባለዋ ሆን ብለው ሴትዮዋ እንዳያረግዙ ከግብረ ሥጋ ግኑኝነት በመቆጠብ እርግዝናን የሚከላከሉበት ዘዴ ነው:: ባለዋ

ሴትዮዋ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተለያይተው ከሆነ ወይንም በሕመም ምክንያት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ስለመፈጸም እንደ ወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ሊወሰድ አይችልም::

10. በግብረ ሥጋ ግንኙነት ጊዜ የወንድን የዘር ፍሬ በሴትዮዋ ብልት ውጭ ማፍሰስ (withdrawal) ሴትዮዋ እንዳታረግዝ ያደርጋታል::

11. ከግብረ ሥጋ ግንኙነት በኋላ ሴትዮዋ እንዳታረግዝ ብልቷን መታጠብ (douche) በወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴነት የሚቆጠረው ሴትዮዋ የግል ንፅሕናዋን ለመጠበቅ የተነሣ የምታደርገውን መታጠብ የማይጨምር ሲሆን፣ ሴትዮዋ የምትታጠበው እንዳታረግዝ ብላ የወንድን የዘር ፍሬ ከብልቷ ለማጠብ የምታከናውነው ሥርዓት ነው::

12. ባህላዊ መድኃኒቶች ወይም ዘዴዎች የተለያዩ አይነቶች ሊሆኑ የሚችሉ ሲሆኑ ዘዴዎቹ ግን ለሌላ ጥቅም ተብለው የሚደረጉ ቢሆኑ ለወሊድ መቆጣጠሪያነት ሆን ተብለው የሚደረጉ ብቻ መሆን ይኖርባታል::

13. ሌሎች ዘዴዎች በወሊድ መቆጣጠሪያነት የሚጠቀሙ ቢኖሩ ከነስሙ የዘዴው አይነት መገለጽ ይኖርበታል:: ለተጠሪዋ የዘዴው ዋና ጥቅም ለወሊድ መቆጣጠሪያነት መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው::

06. ይህ ጥያቄ የሚቀርበው በጥያቄ 604 ወይንም 605 ኮድ 1 ለተሰጠባቸው ዘዴዎች ብቻ ሲሆን ይህም ማለት ከዚህ በፊት ቢቀርብ ስለ ዘዴዎቹ ሰምተን እናውቃለን ብለው ለመለሱት ዘዴዎች ማለት ነው:: በነዚሁ ዘዴዎች ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ተጠቅመው እንደሆነ ተጠይቀው ተጠቅመው ለሚያውቁት ዘዴ ኮድ 1 ሲሰጥ፣ ተጠቅመውበት ለማያውቁት ዘዴ ኮድ 2 ይሰጠዋል::

608. ይህ ጥያቄ በጥያቄ 603 ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ በጥያቄ 603 ላይ የተሰጠው መልስ ለዚህ ላይ ይሠራል::

609. በጥያቄ 605 ላይ አንዱ ዘዴ አንኳን ኮድ 1 የተከበበ ካለ የዚህ ጥያቄ መልስ አዎን /ኮድ 1/ ይሆናል::

610. መልስ ሰጭ በጥያቄ 608 ወይም 609 በአንደኛው ወይም በሁለቱም ኮድ 1 ከተሞላላቸው የዚህ ጥያቄ መልስ ኮድ 1 ይሆናል::

611. በጥያቄ 606 ላይ ለአንዱ ዘዴም ቢሆን ኮድ 1 የተከበበ ካለ የዚህ ጥያቄ መልስ ኮድ 1 ይሆናል::

612. በጥያቄ 607 ላይ ለአንዱ ዘዴም ቢሆን ኮድ 1 የተከበበ ካለ የዚህ ጥያቄ መልስ ኮድ 1 ይሆናል:: ነፍሰ ጡር ለሆኑ ሴቶች የዚህ ጥያቄ መልስ ኮድ 2 ይሆናል::

4. ቤትን በስፕሬሽን ማምከን፤ የአንዱ ስፕሬሽን ዋጋ፣
5. ወንዝን በስፕሬሽን ማምከን፤ የአንዱ ስፕሬሽን ዋጋ፣
6. መርፌ፤ አንዱ ጊዜ ለመውጋት የሚጠየቀው ክፍያ፣
7. የማሠፀን ቁስ፤ የአንዱ ዋጋ፣

ለጥያቄው መልስ የሚመልሰው ቤተሰብ በአሁኑ ወቅት የምትጠቀምበት ዘዴ ዋጋ ወደ ሙሉ ብር ተጣግቶ ይሆናል። ለምሳሌ ለ50 የወሊድ መቆጣጠሪያ ክኒኖች የሚከፈለው ስምንት ብር ከሰባ አምስት ሣንቲም ቢሆን የሚመዘገበው 08 ብቻ ይሆናል። የወሊድ መከላከያ ዘዴው በነጻ የሚገኝ ከሆነ 98 ይመዘገባል።

618. የወሊድ መከላከያ ዘዴዎችን ለማግኘት በጉዞ የሚያጠፉት ሰዓት የሚመዘገበው በደቂቃ ብቻ ነው። ስለዚህ መልሱ በሰዓት ቢነገርም ወደ ደቂቃ ቀይረን መመዝገብ ይኖርብናል። ለምሳሌ ጉዞው አንድ ሰዓት ተኩል የሚፈጅ ከሆነ የሚመዘገበው 090 ይሆናል።

622. ይህ ጥያቄ በአሁኑ ወቅት ዘመናዊ የሆኑ ዘመናዊ ያልሆኑ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ላይ ለሚገኙ ሴቶች ሁሉ ይጠየቃል። ይህም ማለት በጥያቄ 613 ማንኛውንም አይነት መልስ ተመልሶላቸው ለነበሩ ሴቶች ሁሉ ይህ ጥያቄ ይቀርባል ማለት ነው። በዚህ ጥያቄ የሚጠየቀው በአሁኑ ወቅት በመጠቀም ላይ የሚገኙትን የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ቢያደርጉ ለምን ያህል ጊዜ እንደ ተጠቀሙ ቢሆን መልሱ የሚመዘገበው ወደ ሙሉ ወሮች ተጣግቶ ነው። ለአሥራ አምስት ቀናትና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ዘዴውን ለተጠቀሙ 01 ሲመዘገብ ከአሥራ አምስት ቀናት ላነሰ ጊዜ ዘዴውን ለተጠቀሙ 00 ይመዘገባል።

623. ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው ቤተሰብ በአሁኑ ወቅት በመጠቀም ላይ ያሉትን ዘዴ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚጠቀሙበት ወቅት ስንት ልጆች እንደነበሩዋቸው ነው። ዘዴውን ለመጀመሪያ ጊዜ በሚጠቀሙበት ወቅት ምንም ልጅ ካልነበሩዋቸው 00 ይመዘገባል።

642. ለቁጥር 613 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመለከቷል።

643. ለቁጥር 614 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመለከቷል።

647. ለቁጥር 616 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመለከቷል።

656. ለቁጥር 633 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመለከቷል።

**የስልኩ መቆጣጠሪያ ዘዴ ተጠቃሚው ለማያውቅ ነገር ግን**
**በባለስልኩ መቆጣጠሪያ ዘዴ በራሱ ለሚያውቅ የሚጠየቅ**

በ662–669 ያሉት ቁጥሮች የሚቀርቡት በ611 ቁጥር 2 ለተወሰነ ገበያቸው ስለስልኩ መቆጣጠሪያ ዘዴ በራሱ የሚያውቅ ነገር ግን በስልኩ መቆጣጠሪያ ዘዴ ተጠቃሚው ለማያውቅ ቤቶች ነው። ቁጥሮቹ የሚያተኩሩት እስከ ዛሬ ድረስ እንጂ በስልኩ የመቆጣጠሪያ ዘዴ ተጠቃሚው እንደማያውቅ እና ሁኔታ ለመጠቀም ያበረ እንደሆነ ነው።

662. ይህ ቁጥር በሚቀርብበት ወቅት ቤቶቹ የስልኩ መቆጣጠሪያ ዘዴ በመጠቀም ያገኙት የተለያዩ ዕቃዎች በዓይነ የሚዘገበው ግን አዲስ ዕቃዎች ብቻ ቤቶቹ የሚታቀርበው ነው። ይህ ቁጥር በሚቀርብበት ወቅት የቤቶቹ ዕቃዎች ተከፋይ መሆን ስለመሆኑ መመሪያ ሲደገፍ ማመዛዘን ተገቢ አይደለም። ቁጥሩ በሚቀርብበት ጊዜ መረጃ በባቡሮች ማግኘትን ሁኔ የሚታየው መስለው መታየት የለባቸውም። ለአባላ አገሪቷ ቤት አሥራ ሁለት ዓይነት ውስጥ የስልኩ መቆጣጠሪያ ዘዴ የሚተጠቀሙ ተጨማሪ ሰው ለመውሰድ ነው ብሎ በትገለጸ አለፈንግ ቀረታ መረጃ በባቡሩ መልክን ተቀባ መመሪያ ይጠቀልበታል።

663. ለወደፊት በስልኩ መቆጣጠሪያ ዘዴ ለመጠቀም ያበረ እንደሆነ ቤቶቹ መረጃ በባቡሮችን ሳለማስቀየር በሚሊ በሚት "አዲን" የሚል ወሰብ ለገዳይበጡ ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል።

668. ይህ ቁጥር የሚቀርበው በቁጥር 667 ላይ በ1–7 በተዘረዘሩት ዘዴዎች ውስጥ ስለ አንቀጽ ዘዴ በራሱ ለሚያውቅ ቤቶች ብቻ ነው።

ቦታ "ረ" ይሆናል:: የዚህ ጥያቄ መልስ ከጥያቄ 604 እና 605 ጋር ተመሳክሮ አስፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎች ሁሉ ማድረግ ይኖርበታል::

680. ለጥያቄ 678 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

681. ለጥያቄ 679 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

682. በሞት፣ ከባለቤታቸው ጋር በመለያየት፣ ሁዘት. የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳይፈጸም በዓቻ መልሱ ቦታ 2 ይሆናል:: የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም እየቻሉ እርግዝናን ለመከላከል በሚል ምክንያት በቻ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳይፈጸም ቦታ 1 ይመዘገባል:: የዚህ ጥያቄ መልስ ከጥያቄ 606 ጋር ተመሳክሮ አስፈላጊው እርማቶች ይደረጋሉ::

683. እርግዝናን ለመቆጣጠር ከግብረ ሥጋ ግንኙነት የተቆጠቡት በአንድ ጊዜ በላይ ከነበረ የሚመዘገበው ለረጅም ጊዜ በቆየበት ወቅት ለምን ያህል ጊዜ እንዳቋረጡ ነው::

684. ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው ከዚህ በፊት አግብተው ለሚያውቁ ሴቶች ሁሉ ይሆናል:: የሚጠየቀውም በአሁኑ ወቅት እንዳያረግዙ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከመፈጸም በመቆጠብ ላይ እንደሆኑ ቢሆን በተለይ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ያቋረጡት ሆን ብለው ለዚሁ ቁጥጥር እንደሆነ ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የዚህ ጥያቄ መልስ ከጥያቄ 607 ጋር ተመሳክሮ አስፈላጊዎቹ እርማቶች ይደረጋሉ::

685. ይህ ጥያቄ አግብተው ለሚያውቁ ሴቶች ሁሉ የሚቀርብ ቢሆን መልስ ሰጪዎችን የሚያበሳጭ ሊሆን ስለሚችል ጥያቄው ሲቀርብ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል::

ከሚፈልጋቸው ሴቶች ጋር የማይጣጣም ሊሆን ይችላል። ለሶሻሌ አዶር የወለዱ ቤት የሚወልዷቸውን ሴቶች ብዛት መወሰን ቢችሉ ኖሮ በዉበት ቢወሬዱ ይመርጡ እንደነበር ሊያስመዘግቡ ይችላሉ።

715. ይህ ጥያቄ ከዚሁ በፊት ወለደቀቻው ከነበሩ ወንዶችና ቤቶች ሴቶች ወይንም በተጨማሪ ለመዉለዱ ከሚፈልጋቸው ወንዶች ወይንም ቤቶች ሴቶች ብዛት ጋር ባይያያዝ በተለይ የሚዘየቀ ነው።

# የ1982 የልደትና ቤተሰብ የሙከራ ጥናት የመረጃ ሰብሳቢዎች ዕለታዊ የሥራ፣ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ

ክፍል–1 **የአካባቢ መለያ**

የቅጽ ቁ.______

| 1. አስተዳደር አካባቢ/ራስ ገዝ | | | 2. አውራጃ | | | 3. ከተማ | | | 4. ቀበሌ/ገበሬ ማህበር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | |
| ////// | 1 | 2 | ////// | 3 | 4 | ////// | 5 | 6 | ////// | 7 | 8 | 9 |

ክፍል–2 **የመረጃ ሰብሳቢ ዕለታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት**

| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የቤተሰብ መጠይቅ | | | የሴቶች መጠይቅ | | |
| የቤተሰብ ተራ ቁጥር | የቤተሰብ ኃላፊ ስም | ውጤት | መጠይቁ የተሞላበት ቀን | አስተያየት | ውጤት | መጠይቁ የተሞላበት ቀን | አስተያየት |
| 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 |
| | | | | | | | |

ለዓምድ–7 የተሰጡ መልሶች

1. መጠይቁ ተጠናቋል
2. አቤት አልተገኘም
3. ቤተሰቡ ለሥራ ወይም ዘመድ ጥየቃ ሌላ ቦታ ሄዷል
4. ምዝገባው ተላልፏል
5. አልተባበረም
6. ቤተሰቡ ለቆ ሄዷል
7. መኖሪያው ፈርሷል
8. ቤት አልተገኘም
9. ሌላ/ይገለጽ/ ________

ለዓምድ–9 የተሰጡ መልሶች

1. መጠይቁ ተጠናቋል
2. ቤት አልተገኘም
3. ምዝገባው ተላልፏል
4. አልተባበረም
5. በከፊል ተጠናቋል
6. ሌላ/ይገለጽ/ ________